የዛሬዋ ኢትዮጵያ የጥንቷም ኢትዮጵያ ናት

የዓለምን ሁሪያ ስንመለከት የማዕዘነ ምድር አቀማመጥ የተለያየ ቅርጽን ይዞ እንደ ሙግኖቱ መጠን የሰው ልጅ ሕይወትም ይህኑ አቀማመጥ ተከትሎ ይቀኛል፣ ከዚህም የተነሣ ምንም እንኳን የሰው ልጆች በሰው ልጅነታቸው በመከከላቸው ምንም ዓይነት የተፈጥሮ ልዩነት እንደሌለ ቢታመንም የተሰራጨበት አካባቢ አቀማመጥ (ቆላ፣ ደጋ፣ ወይና ደጋ) የአየር ጠባይ (ሞቃታ፣ ብርዳማ፣ ነፋሻ) ተጽዕኖ የመነጨ የአኗኗር ዘይቤና የቀለም ዓይነት ልዩነት ይታይባቸዋል።

ስለዚህ የአካባቢያችንና የአካባቢ ነዋሪዎች ስያሜያች ብዙ ጊዜ ከዚህ ሁኔታ ጋር አየተያያዙ ይገኛሉ ለምሳሌ ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ (ቅጽላዊ ስም) ከሰው ልጆች መከከል የተወሰነው ዘርዓ ትውልድ ከተሰራጨበት አካባቢ የአየር ጠባይ ተጽዕኖ ከተፈጠረ የቆዳ ቀለም ጋር የተያይዘ የተሰጠ ስያሜ መሆኑና ኢትዮጵያም የሚኖሩበት አካባቢ ስም ለመሆን እንደቻለ ተዳጋግሞ ተነግሯል። እንግዲህ ከዚህ መሠረት ሐሰብ በመነሣት የተነሣንበትን ጥሬ ነገር ስንመለከት ከሞንት የታሪክም ሆነ ከቅዱሳት መጻሕፍት በመነጠ መረጃነት "ኢትዮጵያዊ፣ "ኢትዮጵያውያን" ፣ "ኢትዮጵያ" የሚለውን በሦስት ከፍሎ ማየት የታሪኩን ትክክለኛ ሥዕል ለማስቀመጥ የሚያስችል አጋጣሚ ነው የሚል እምነት አለን።

- ዘርዓ ትውልድ
- መልክዐ ምድር
- የጡጭ ማንነታት(የአካባቢውና የኢትዮጵያ)

ሀ - ዘርዐ ትውልድ

የሰውን ልጅ ተፈጥሮ በተመለከተ የሰው ልጅ በመሉ የአንድ አዳም ልጅ መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት የተረጋገጠ ቢሆንም ኪሚኖርበት አካባቢ የአየር ጠባይ (የጊዜ ርዝመት) የተነሣ የቀለም ልዩነት ይታይበታል። ከዚህም በመነሣት ኢትዮጵያውያን ማለት መልክ ጠይም ዘርዐ ትውልድ ማለት ሲሆን ኢትዮጵያ ማለት ይህ መልክ ጠይም ዘርዐ ትውልድ የሚኖርባት አካባቢ ማለት ነው። ወደ ሥርወ ቃሉ ስንመጣ ከሞንት የግሪክና የሮማ ታሪክና መልክዐ ምድር ሊቃውንት ለመርዳት እንደምንችለው ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከሁለት የግሪክ ቃላት የመጣና ትርጉሙም ይኸው መልክ-ጠይሞች የሚኖሩበት አካባቢ ማለት ሆኖ ይገኛል።

ከሞንት ሊቃውንት መከከል ቅድመ ክርስቶስ 400 -300 ዓመት አካባቢ የነበረው የታወቀው ግዮም ጣጣሚው ግሪክ ሆሜር (ኦሚሮስ) ለመጀመሪያ ጊዜ በግሪክ ሥነጽሑፍ (ሥነ ግዮም) ኢትዮጵያውያን የሚለውን ቃል ነበር የተጠቀመ ሆሜር በዚሁ ግዮሙ (ሁለት ጊዜ በኢሊያዳና ሦስት ጊዜ በኦዲሲያ) ጠቅሷል፣ ስለ ኢትዮጵያውያንና ስለሚኖሩበትም አካባቢ ሲገለጽ ኢትዮጵያውያን ደኃትና መልከም (ሰምች) እንደ ሆኑ የሚኖሩበትም አካባቢ የምድር ጻርቻና ፀሐይማ መሆኑን ተናግሯል። በዚህ ዓይነት ሆሜር በምድር ጻርቻ ስለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሲናገር እንርሱም ከፈጠሯቸ በፀሐይ መግቢያ (ምዕራብ) አቅጣጫ ግማሾቹ ደግሞ በፀሐይ መውጫ (ምሥራቅ) አቅጣጫ እንደሚኖሩ በመግለጽ ኢትዮጵያ የትኛውን ማዕዘነ ምድር አካባቢ እንደምትይዝ ለማመልከት ሞክሯል።

እንግዲህ ሆሜር በምድር ጻርቻ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሲል የትኛውን የምድር ጻርቻ አከባቢ ማለቱ ነውን ይህን የሆሜርን አነጋገር በትክክል መረዳት የምንችለው በተከታታይ የተጻፉትን የታሪክና የመልክዐ ምድር ሊቃውንት አመለካከት በመገንዘብ ነው፣ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት የመልክዐ ምድር ማለትን ስፋቱ ከግብጽ ደቡብ አስከ ሕንድ የሚደርሰው አካባቢ በጊዜው የመልክዕ ምድር ግንዛቤ የምድር ጻርቻ መሆኑን ነበር ሆሜር የተመለከተው። ነገር ግን ይህ የሆሜር አጻጻፍ የበሰለ ግልጥ እየሆነ የመጣውና የኢትዮጵያን መልክዐ ምድርና ሥነ ሰብአዊ መልክ በቅርብ ለጠመርመርና በትክክል ለመታወቅ ሁኔታው አመች ሆኖ የተገኘው ከሂሮዶቱስ ጊዜ ጀምሮ ነው።

ቅድመ ለዲት ክርስቶስ ከ400 — 300 ዓመት የነበረው ይህም ዕውቁ ግሪክ ታሪክ ጸሐፊ ሄሮዶቶስ በመከከለኛው ምሥራቅ ጉዞ አደርጎ በተለየ በግብጽ ባርከት ላለ ጊዜ የተቀመጠ በመሆኑ ስለኢትዮጵያ ከተጻፉየ ምንጮች በቂ መረጃ ለማግኘት የቻለ ሰው ነበር ከዚህ ከአገኘው መረጃ በመነሣት ኢትዮጵያን በሁለት ከፍሎ ለማየት ሞክሯል። አንደኛው ኢትዮጵያ ከግብፅ አትራቢያ አካባቢ የምትገኘው ስትሆን ሁለተኛዋ ኢትዮጵያ ደግሞ ወደ ደቡብ የተዘረጋው የአሁኑ የኢትዮጵያ አካባቢ ነበረች ማለት ነው በሩቅ አካባቢ ስለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም ጽፏልና።

በዚህም ጽሑፍ እንዚህ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት ሩቅ ሀገር ከግብፅ ደቡብ መለስ የሚገኝና ቀይ ባሕርን ተከትሎ የሚሔድ አካባቢ እንደነበረና የአነዚህን ኢትዮጵያውያንም ኖሮ ዘዴ ሲገልጽ ሣዕድሚ ባለጸጋዎችና ጭነ ተመጋቢዎችም እንደነበሩ ያስረዳል። እንግዲህ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያውያን የአንድ የተወሰነ ዘርዐ ትውልድን የሚያመለክት(የሚያሳይ)ስም ሲሆን ኢትዮጵያም ከዚሁ ዘርዐ ትውልድ ስም የመነጨ የአንድ የተወሰነ አካባቢ ስም ነው።

በዚህ መልክ በአንድ በኩል ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያውያን የሚለው ቅጽላዊ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆሜር በቋሞታ ለዚህ ሕዝብና አካባቢ የተሰጠ ሆኖ ሲገኝ በሀገራችን የታሪክ ሊምድ ደግሞ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት አንድ ጊዜ በኢትዮጵያ ነግሦ ከንበረ ኢትዮጲስ አንደኛ ከሚባል ንጉሥ የመጣ ስም እንደሆነ ተነግሯል።

ግን በልሳ በኩል ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስንመለስ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ የዕብራይስጥ ኩሽ የሚሪክ ትርጉም ሆኖ ይገኛል። በዕብራይስጡ ኩሽ የሚለው ቃል በሦስት ትርጉሞች ይገለጻል። አንደኛው ትርጉም የተጻፈውያ ስም መሆኑ ነው፣ ክፍም ልጆች ማካከል አንዱ ኩሽ ይባል እንደነበር ይታወቃል (ዘፍጥረት 10፡6) ሁለተኛው ትርጉም የጎጉድ ኩሽ ወይም ኩሻዊያን ተብለው እንደሚጠሩ ይታወቃል፣ በሌላ በኩል ደግሞ መልክ ጠይም ወይም ጥቁር ሰሆነው ሰው የተሰጠ ስያሜ ሆኖ ተገኝቷል፣ በዚህ ትርጉም መልክ ጠይም ሕዝቦች ሁሉ የኩሽ ዘሮች ናቸው ብሎ መናገሩ ደግሞ ያስቸግራል፣ ሦስተኛ ትርጉም የአካባቢ ስም ሆኖ መገኛቱ ፣ መልክ ጠይም ሕዝቦች የሚኖሩበትና ከጣበስ ደቡብ እስከ ሕንድ ያለው አካባቢ መጠሪያ ስም ሆኖ ተገኝቷል። ስለዚህ ኩሽ በሁለተኛው ትርጉም የተመለከተው ዘርዐ ትውልድና በሦስተኛው ትርጉም ደህ ዓይነት ዘርዐ ትውልድ የሚኖርበት አካባቢ ስም ሆኖ ይገኛል።

እንግዲህ በእንድ በኩል የኩሽንና በሌላ በኩል የኢትዮጵያዊነና ኢትዮጵያ መሰልነት እንዴት እንደተፈጠረ ዋያቱ መነሣት የሚጠበቅ ነው። ብሉይ ኪዳን ትድመ ልደት ክርስቶስ ከ1500 — 400 መካከል የተጻፈ መሆኑ ሲታመን በ-284 ከልደት ክርስቶስ በፊት አካባቢ በሰብዓ (70) ሊቃናት ወደ ግሪክ ቋንቋ እንደተተረጎመም ይታወቃል፣ ሰብዓ ሊቃናት በዕብራይስጥ "ኩሽ" የሚለውን ቃል ወደ ግሪክ ቋንቋ " ኢትዮጵያዊ - ኢትዮጵያ" በማለት መልሰውታል።
ስለዚህ ቀጽም ሊል በብሉይ ኪዳን ከመሳ ጀምሮ ኩሽ በመባል ኢየተጠራ በቅላም በታሪክ ዘሥሜር ጀምሮ ኢትዮጵያ - ኢትዮጵያዊ በመባል ይታወቀው ስም አካባቢንና በውስጡ የሚኖሩትንም ሰዎች የሚያመለክት መሆኑ ግልጥ ነው።

እንግዲህ ከታሪክና ከመልክዐ ምድር አሳማመዋ እንደተረዳነው ሁሉ በብሉይ ኪዳን (በዕብራይስጥ) ኩሽና በታሪክ (በግሪክ) ኢትዮጵያዊ ዘርዐ ትውልድን ለማመልከት የተወሰደ ስም መሆኑ በግልጽ የሚታይ ቢሆንም አንዳንድ መረጃዎችን ማየት አስፈላጊ ይሆናል።

1. "ኢትዮጵያዊውም ዝሬ አንድ ሚሊዮን ሰዎችንና ሦስት መቶ ሠረገላዎችን ይህ መጣበቸው ወደ መራሳም መጣ" 2ተኛ ዜና መዋዕል 14፡9
2. "እግዚአብሔርም በአሳና በይሁዳ ፊት ኢትዮጵያውያንን መታ ኢትዮጵያውያንንም ሸሹ" 2ተኛ ዜና መዋዕል 14፡12
3. "ኢትዮጵያዊያን የሊቢያ ሰዎች እጅግ ብዙ ሠረገሎችና ፈረሶች የነበሩአቸው እጅግ ታላቅ - - - ጭፍራ አልነበሩምን?" 2ተኛ ዜና መዋዕል 16፡8
4. "ኢትዮጵያዊያን አጠቡብ የሚኖሩትን የወረዛውያንን መንረስ በኢዮራም ላይ አስነሣ" 2ተኛ ዜና መዋዕል 21፡16
5. "ዘውጉ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ ይቻላልን?" ኤርሚያስ 13፡23
6. "የንጉሥ ቤት የነበረው ጃንደረባ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ኤርሚያስን በጕድጓድ ውስጥ እንዳሠሩት ሰማ" ኤርሚያስ 38፡7
7. "ንጉሡም ኢትዮጵያዊውን አቤሜሌክን ከአንተ ጋር ሠላሳ ሰዎችን ከዚህ ውሰድ" ኤርምያስ 38፡10
8. "ኢትዮጵያዊውም አቤሜሌክ ኤርምያስን ይህን አሮጌ ጨርቅና ዕላቂውን ልብስ ከብብትህ ከገመድ በታች አድርግ አለው —" ኤርምያስ 38፡12
9. "ሂድ ለኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ እንዲህ በልው" ኤርምያስ 39፡16
10. "መልእክተኞች ተዘልለው የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያንን ለማስፈራራት ከፌት በመርከብ ይወጣሉ" ሕዝቅኤል 30፡9
11. "አናንተም ኢትዮጵያውያን ደማሞ በሰይፍ ትገደላላችሁ" ሶፎንያስ 2፡2

ለ/ መልክዐ ምድር

ቀጀም ብለን እንደተመለከትነው ሠሜር ስለ ኢትዮጵያውያን ጠባይና ስለሚኖሩበትም አካባቢ ተናግሯል ሆኖም የሚኖሩበት አካባቢ ሩቅና በጣም ሞቃት ስፍ እንደሆነ ከመግለጽም አልፎ ኢትዮጵያ የሚለውን የአካባቢ ስም አልለጠም (አልተጠቀመም) ነገር ግን ከሠሜር ቀጥሎ የተነሡት ሊቃውንት ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ሀገር መሆኗን በማያሻማ ሁኔታ ከማስረዳታቸውም በላይ ስለ መልክዐ ምድሯ አቀማመጥም በትክክል ለመግለጽ ሞክረዋል። ስለዚህ ከታሪክና መልክዐ ምድር አንጻር ታላቁ የታሪክ ጸሐፊ ሄሮዶቶስና የመልክዙ ምድር ሊቅ የነበረው ስትራቦ ቅድሚያ ቦታን ይዘው ይገኛሉ።

ሄሮዶቶስ ከላይ እንደተመለከትው ወደ መካከለኛው ምሥራቅ መጥቶ በተለይ በግብፅ ብዙ ጊዜ የቆየና ከአካባቢው ዐዋቂዎች ጋር በመወያየት ስለኢትዮጵያ ብዙ ነገሮችን ለመረዳት ችሎ የነበረ ሰው በመሆኑ በዚህም በአሳንው ማሰረጃ መሠረት የኢትዮጵያ ወሰን ከግብጽ ደቡብ ጀምሮ እስከ ሲናሞሞፎሩስ (ሕንድ ውቅያኖስ መጸረሻ) ድረስ እንደነበረ ከዚህም ጋር ኢትዮጵያ ሁለት ክፍሎችን የያዘች አካባቢ መሆኗን ሲያመለክተ እነዚህም አንደኛዋ ከግብጽ ጋር የተጎራበተችው ኢትዮጵያ ሁለተኛዋ ኢትዮጵያ ደማሞ አሣ ተመጋቢዎች ኢትዮጵያዊያን የሚኖሩበት ወደ ደቡብ የተዘረጋችው ኢትዮጵያ (የዛሬዋ ኢትዮጵያ) በአጠቃላይ ግን አንዲት ኢትዮጵያ መሆኗን ገልጿል።

ለትራቦ የኢትዮጵያ ድንበሮች በሰሜን ግብጽ (የኢትዮጵያና ግብፅ ወሰን ኢሲፋንታይን በደቡብ ሲናሞሞፎሩስ (የሕንድ ወቅያኖስ መጸረሻ) እንደነበሩ ሲጽፍ ስለዚህም ሁኔታ መነሻ ምንጮች የሌሎች ሊቃውንት አራቶስቴኒስ (Aratosthenes)

አጋታሪኪደስ (Agathrchides) እና ሌሎች ቀደምት ጸሐፍት ጽሑፎች እንደነበሩም ይታመናል።ሰለ ወባይ ወንዝም ሰጽፍ ይህ ወንዝ ከኢትዮጵያ ድንበሮች ተነሥቶ ወደ ሰሜን የሚፈስ ቡተለይም የሚመነጨው ከአንድ የኢትዮጵያ ሐይቅ (ማና ሐይቅ) መሆኑን ይገልጻል፣ እንደዚሁም የሦስቱንም የወባይ ወንዝ መጋቢ ወንዞችን አስታቡስ (Astabus) አስትሮባስና (Astrobas) አስታሶባስን (Astasobas) አመልክቷል።

ሩአደር እንደ ሄሮዶቱስ ኢትዮጵያ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ አካባቢን የያዘ ሀገር መሆኑን ሲያመለክት በዚህም መሠረት እንዱ ከግብፅ አስከ መርዌ ያለው ክፍል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከመርዌ በመለስ ወደ ደቡብ ምሥራቅ የተዘረጋው አካባቢ እንደነበር ሲያመለክት በተለይ በደቡብ በኩል ያለው አካባቢ ወሰኑ የማይታወቅ ቢሆንም የዓባይ ሁለት መጋቢዎች ወንዞች (ሀሰቴን ወባዮች) የሚይዘውና ቀይ ባሕርን የሚከተለው ክፍል እንደ ነበር ይጽፋል በሌላ በኩል የወባይ ወንዝ ከኢትዮጵያ ሩቅ ክፍለ ግዕዘን ከትልቅ ተራራ ሥር እንደሚመነጭም ርዝመቱ ከመነሻው እስከ መድረሻው 12ሺ ማይልስ እንደሚደርስና አሁንም ሦስት መጋቢ ወንዞች እንደ ነበሩት ሰማሰረዳት ሞክሮአል።

ሮማዊው የመልክዐ ምድር ሊቅ ፕሊኒ ኢትዮጵያ በሰሜን ከሴዶን (አሰዋን) በምሥራቅ ከሙቅያኖስና በምዕራብ ከሊቢያ ጋር እንደምትዋሰን ሲገልጽ በደቡብ ግን ያሉትን ወሰን ለማወቅ እንደአልቻለ ሲያመለክት አቀማመጫ (ቅርጿ) ወደ ደቡብ በሚመለከተው አቅጣጫ ማለክሌንት በደቡብ ምሥራቅ ወደ ደቡብ ምዕራብ አዘነበለ እንደ ነበር ከመርዌ ጀምሮ እስከ ሙቅያኖስ ድረስ በባሕርና በየብስ ያለውን ርቀት ጉዞ አመልክቷል።

የወባይ ወንዝ ሦስት መጋቢ ወንዞች አስታቡስ (Astabus) (ጥቁር አባይ) አስትሮባስ (አትባራ) (Astrobas) እና አስታሶባስ (Astasobas) (ንጭ አባይ) በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያን አቋርጦ የሚሄደው ወንዝ ወይም ከዚጋው የሚመነጨው ጥቁር ወባይ አስታብስ በግራ በኩል የሚፈሰው አትባራ (አስትሮባስ) በቀኝ በኩል የሚፈሰው ወንዝ ነጭ ወባይ አስታሶባስ መሆናቸውን ያመለክታል። የኢትዮጵያ ወሰኖች (ድንበሮች) በሙሉም አቅጣጫ በደንብ ለማልከት የቻለው የመልክዐ ምድር ሊቅ የንበረው ፕቶሎሚያስ ከሳሙዔሮስ ነበር። በዚህም መሠረት ክግብጽ ቀጥሎ (በታች) የምትገኘው ኢትዮጵያ በሰሜን ከግብጽና ሊቢያ በምዕራብ ከሊቢያ ውስጣዊ ማዕዘን አንደምትዋሰን አመልክቷል እንደዚሁም ምንም እንኳን በሰታ አቀማመጥና ስም ከስተራቡ ጋር ቢሰይም ወባይ ከኢትዮጵያ አንድ ሐይቅ እንደ ሚፈስ አመልክቷል። አሁንም (በቀለሞስ) ፕቶሎሚያስ ከሳሙዔሮስ የኢትዮጵያን የባሕር ከተማ የነበረችውን አዶሊስን በኢትዮጵያ ካርታ አስፍሮና እንደዚሁም በተጨማሪ በኢትዮጵያ የነበሩትንና የታወቁ ከተማዎች ከሌንና አክሱምን መገኛበ ይገኛል በተለይ አክሱም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ (መዲና) እንደነበረች ይተርካል።

እንግዲህ በተለይ በግብጽ ከፕቶሎሚያስ በመነ ግዜት ወዲህ ከግሪክነት ዘመን (ሄሊነስቲክ) ዘመን ጀምሮ አይለዩና እየቆየ በኢትዮጵያና በመካከልኛው ምሥራቅ የነበረው ግንኙነት የበለጠ እየተቃረበ ለማምጣት በመቻሉ ይህን አካባቢ በሚመለከት ስለ መልክዐ ምድርም ሆነ ስለ ዘርዐ ትውልድ የሚገኘው እውቀት በማም ግልጽ እየሆነ ነበር ሊታይ የቻለው። ስለዚህ ከፓፒርና ከአንድ አንድ ሌሎች ጽሑፎች (ስልተው የሚታዩም እንኳን ሰመሆን ባይኾሉ) መረጃዎች ተገኝተዋል። ለምሳሌ "ግዕዱተ ኤርትራን (periplus of erythrean sea) የጻፈው ሰው ሰለአክሱም ግዛትና ስለንበረው የንግድ እንቅስቃሴ የሰጠው መረጃ ልክና ዐቂ ነበር።

የኢትዮጵያ ግዛት በደቡብ ከሞስኮፋጊ (Moschophagi) (ባዕላቲ - እንስሳ) ሀገር በልሚን እስከ በርበር (በርበራ) ይደርስ እንደ ነበርና በምሥራቅ ወሰኑ ቀይ ባሕር እንደነበር ይጽፋል። ሩፊኖስ በወራተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ብኢትዮጵያ ዘአክሱም የክርስትና እምነት እንደገባና ቤተ ክርስቲያን እንደተመሠረተች በግልጽ አትቷል። ከዚህም በመቀጠል በተለይ ስለኢትዮጵያ ዘአክሱም የንግድ የሥነ ፅሁፍና የፖለቲካ ሁኔታዎችን በዝርዝር ሰመመዝገብና ሰመጻፍ ሰለዚህ አካባቢ በቂ ሰመረጃዎችን ሰማግኘት ችሏል።

አጻዊ ውቅያኖስ ቶማስ (Indopleutis) በክርስቲያናዊ ሥዕሰ ምድር ስለኢትዮጵያ ዘአክሱምና አካባቢው የፖለቲካ የንግድና ሥነ ጽሑፍ እንቅስቃሴ በሰፊው ያስረዳል፣ ከዚያም ወዲህ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በተከታታይ በተለይ ክቢዛንቲን ጋር ስለነበራት ግንኙነት በሰፍው ጽፏል። የዲዮስግሪክ ግንኙነትና ልውውጥም አበውትር የሚካሂድና የተጠናከረም እንደ ነበር ለማስረዳት ሞክሮአል፣ በዚህ ሁኔታ ቀስ በቀስ ኢትዮጵያ የሚሰው ሰምና አጠቃላይ የአካባቢው ግንባቤ (ቅርጽና መንፈስ የዛሬዋን ኢትዮጵያ አየሸፈነ እና አያማከለ ወደ ጊዜአችን ደርሷል።

በአሁኑ ጊዜ ስለጥንታዊ ኢትዮጵያ በአጠቃላይ የተነገረው ሁሉ ቅሪት በመግኘት የሚታየውን ለማስታወስም የሚቻለው በሀገሪቱን ላይ ከአለው የባህል፣ የቋንቋ የሃይማኖት ሀኔታዎችና ይዘቶች ጋር ተገናዝበ ብቻ በመሆኑ የዛሬዋ ኢትዮጵያ የጥንቷ የታሪክና የመልክዐ ምድር ኢትዮጵያ እንደሆነች በግልጽ የሚታይ ሐቅ ነው። እንግዲህ እነዚህ ምንጮችና መረጃዎች ላይ በመነሳት ከታሪክና ከመልክዐ ምድር አንጻር ኢትዮጵያ የሚለውን ስም የያዘው አካባቢ ከግብጽ ደቡብ ጀምሮ ያለው የጠይም ሕዝቦች አካባቢ መሆኑን መረዳት ይቻላል። አሁንም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስና በዕብራይስጥ "ኩሽ" በግሪክ ትርጉም "ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል የአካባቢ ስም መሆኑን ከተለያዩ ጥቅሶች መገንዘብ ይቻላል። ስለዚህ በታሪክና በዘርዐ ትውልድ መልክ እንደተመለከትነው ሁሉ የዕብራይስጥ "ኩሽ" እንደዚሁም ከመልክዐ ምድር አንጻር ከግብጽ ደቡብ ጀምሮ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ያለውን አካባቢ ያመለክታል።

ስለዚህ የሚከተሉትን ጥቅሶች በመመልከት በትክክል መመረተ ሐሳቡን መረዳት ይቻላል።

1. "የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴርሐቅ ሊወጋህ መጥቶአል" 2ኛ ነገሥት 19፡9።
2. "ከአርጤክስስም በመን እንዲህ ሆን ይህም አርጤክስስ ከሕንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በመቶ ሃያ ሰባት አገሮች ላይ ነገሠ" አስቴር 1፤1።
3. "ከሕንድ ጀመሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በመቶ ሃያ ሰባት አገሮች ላሉ ሹማምንትና አለቆች . . " አስቴር 8፡9።
4. "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" መዝሙረ ዳዊት 66:31
5. "እነሆ ፍልስጤምማሪያን ጢሮስም የኢትዮጵያ ሕዝብ" መዝሙረ ዳዊት 87:4
6. "የኢትዮጵያ ጥቃዞን አይሰጥባትም ቢዋሩ ወርቅ አትሻሙትም" ኢዮብ 28:19
7. "ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ላሉች ክንፍ ያላቸው መርከቦች" ኢሳያስ18፤1።
8. "በግብፅና በኢትዮጵያ ላይ ሦስት ዓመት ለምልክትና ለተአምራት ሲሆን ራቁቱንና ባዶ እግሩን እንደሄደ እንዲሁም የአሶር ንጉሥ የግብፅና የኢትዮጵያን ምርኮ . . . " ኢሳ. 20፡3።
9. "የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴርሐቅ ሊዋጋህ መጥቶአል" ኢሳይያስ 37፡9።
10. ". . . ኢትዮጵያንና ሳባንም ለአንተ ሩንታ ሰጥቻለሁ" ኢሳይያስ 43፡3።
11. "የግብፅ ድካምና የኢትዮጵያ ንግድ ቁመት ረጅሞችም የሳባ ሰዎች ወደ አንተ ያልፋሉ . . ." ኢሳ. 45፡14።
12. "ኢትዮጵያና ፋጥ ሉዳም የተደባለቀም ሕዝብ ሁሉ ኩብም . . ," ሕዝቅኤል 30፡5።
13. "ፋርስንና ኢትዮጵያን ፋጥንም ከእነርሱ ጋር ጋሻና የራስ ቁርን የለበሱት ሁሉ" ሕዝቅኤል 38፡5።
14. "በክበረችም በግብጽ ፅታ ሁሉ ላይ ይሠለጥናል የሊቢያና የኢትዮጵያ ሰዎችም ይከተሉታል" ዳንኤል 11፡43።
15. "ኢትዮጵያና ግብጽ የማይቆጠር ታይልዋ ነበሩ ሩጥና ሊቢያ ረዳቶችዋ ነበሩ" ናሆም 3፡9።
16. "ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ሊቀች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል" ሶፎንያስ 3፡10።

ሐ/ የአካባቢ ግንኙነት (አካባቢውና ኢትዮጵያ)

በመጽሐፍ ቅዱስ (ብሉይ ኪዳን) በሰብራይስጥ "ኩሽ" ወይም በግሪክ "ኢትዮጵያ" የሚለው አካባቢ ከአጎረባች አካባቢዎች (አገሮች) ጋር ማለት እንደ ወረቢያ ሩርስ እሥራኤል ግብጽና ሊቢያ ከመሳሰሉ አገሮች ጋር የተቀራረበ ግንኙነት እንደነበረው በብሉይ ኪዳን ተጽፎ ይገኛል። ይህም ዓይነት ግንኙነት የንግድ ልውውጥን የባህል መተግበርን የአምልኮት መወራረስን እንዳስተለ መረዳት ይቻላል። ይህንንም በትክክል ማረጋገጥ የምንችለው ቀደም ባሉት ጊዜያት በእነዚህ አካባቢዎች በጎሳብት የንግድ ልውውጥ ዕቃዎች ለምሳሌ ዕጣን፣ ከርቤ፣ የአምልኮትና የባህል ዕቃዎች ለምሳሌ ጸናጽል ከበሮ የመሥዋዕት ማቅረቢያ ዕቃዎች ንዋየ ቅድሳት ወዘተ የሚታዩ ዓይነቶች ናቸው፣ ይህን ሁሉ ማስረዳት የሚችለው ስለዚህ ሁሉ ታሪክ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ባለቤት ሆና መገኛቷ ነው።

በጥሬይ ኢትዮጵያ ቀደም ብላ የአንድ አምላክ እምነት ተከታይ እንደነበረች ስለዚህም "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" ከሚለው ጥቅስ እንደ ታሪክ ጸሓፊው ባጅ በመሳሣት ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን የማታውቅበት ጊዜ እንደአልነበረ ይተረካል። ስለዚህ ብዙ የታሪክ ሰነዶችና የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች አሉ፣ ለምሳሌ ከብሉይ ኪዳን ንግሥት ሳባን(1ኛ ነገሥት 10፡1-13, 2ተኛ ዜና መዋዕል 9፡1-12) ክሉዲስ ኪዳንም ንግሥት አዜብን (ማቴ 12፡42 ሉቃ 11፡31) መመልከት በቂ ምስክር ነው።

ንግሥት ሳባ ወይም ንግሥተ አዜብ በአንድ አምላክ የምታምን የኢትዮጵያ ንግሥት እንዲያውም የነፈዋ ኢትዮጵያ አካባቢ ንግሥት እንደነበረች በታሪክ የተረጋገጠ ነው። ንግሥቲ ሳባ በሀገሯና በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች መካከል ዳብሮ ከነበረው የንግድና ሌላም ዓይነት ግንኙነት የተነሣ ስለዚህ አካባቢ በቂ ዕውቀት ሊማግኙት ችላ እንደ ነበር ይታመናል። በተለይ የኢየሩሳሌም ንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብና ዝና ሰምታ ስለነበር ሄዳና በአገሯ የነበረና ታይቶ የማይታወቅ ብዙ ሽቱን 120 መክሊት ወርቅን የከበረ ዕንቁ አስጭና ሄዳ የሰሎሞንን ጥበብ ለመሳብየት እንደቻለች በጉብኝትዋም ጊዜ የመንግሥቱን አስተዳደር የቤተ መንግሥቱን ሥነ ሥርዓትና የሠራዊቱን ሕግና ሥርዓት ተመልክታ ለሰሎሞን ይህን ጥበብና ዕውቀት የገለጸለትን አምላክ እንደ አመሰጋገንና በሂደችበት ሁኔታ ወደ ሀገርዋ እንደተመለሰች መጽሐፍ ቅዱስ (ከላይ በተመለከትት ጥቅሶች) ሊናገር በቃል ሲያያዝ እንደመጣውና በታሪክ መጽሐፍትም ሰፍሮ እንደሚገኘው ደግሞ ንግሥቲ ሳባ ብሉይ ኪዳንን ተቀብላ ወደ አገርዋ እንደተመለሰች ሲተረክ የኡሪትም አምነት በኢትዮጵያ ተሰራጭቶ እንደኖረ ከዚህም እምነት ጋር የተያያዙ ባሕሎች በአገራችን ሰፍረው እንደቆዩና እስከ አሁንም በክርስትና እምነት ባህል ውስጥ በመታቀፍና በመዋሐድ ተሰራጭተው እንደሚገኙ መረዳት ይቻላል። ስለዚህም እንደ ግዝረት በዓል አከባበር የቤተ መቅደስ አሠራር ቅርጽ ወዘተ የመሳሰሉት የአገራችንን ባሕሎች መመልከት በቂ ምሳሌ ነው።

በዚህ ዓይነት ከሞንት አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አሪትን የተቀበለች አገር ስትሆን ከዚህም በመነሣት ሕዝቦጅ "ሮስተ እግዚአብሔር" እየተባሉ ይጠራሉ ኢትዮጵያ ክርስትናንም ለመቀበል የመጀመሪያዋ አገር ሆና ተግኝታለች። በሐዲስ ኪዳን (ግብረ ሐዋርያት 8: 26- 39) እንደሚነበበው የንግሥተ ኢትዮጵያ ባለሟል (ሐፅዋ ለሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ) በአሪት ሕግ መሠረት የሩሲካን በዓል ለማክበርና ለመሰገድ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሲመለስ በመንገድ ከጻያቅን ፊልጶስ ጋረ ይገናኛል በሚገናኙበትም ጊዜ ባለሟሉ ቅንቢተ ኢሳይያስን(53፣ 7-8) "እንደበግ ወደ መታረድ ተነዳ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም በውርደት ፍርድ ተወገደ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና ትውልዱንስ ማን ይናገራል?" የሚለውን ክፍል ያነብ ስለነበር ፊልጶስ ይህ ጥቅስ የሚተነብየው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ

እንደ ነበርና ይህም ትንቢት የተፈጸመ መሆኑን ስለሰበከለት እሱም ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አመኖና ተጠምቆ ወዴ አባሩ እንደ ተመለሰ ይታመቃል። ስለዚህ የጥንት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ለምሳሌ እን አውጉስቲኖስ እንደሚጽፉት ክርስትናን ተቀብሎ የተጠመቀው ከሐዋርያት ቀዋሎ የመጀመሪያው ሰው ይህ የንግሥተ ኢትዮጵያ ባለሟል ሲሆን ከኢየሩሳሌም ውጪ ክርስትናን የተቀበለች የመጀመሪያ አገር ኢትዮጵያ መሆኗን አረጋግጠዋል።

ማጠቃለያ

እስከ አሁን "ኢትዮጵያውያን" ከማዕዘን ምድር አንዱን ክፍል የያዙ ሕዝቦች መሆናቸውንና የያዙትም አካባቢ "ኢትዮጵያ" እንደሚባል ተመልክተናል። በዚህ ታሪካዊ ሁኔታ በመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ የሚለው ስም የአንድ ዘርዐ ትውልድ የወል ስያሜና ኢትዮጵያዎም የዚህ ዘርዐ ትውልድ አካባቢ ስም መሆኑን አይተናል። ነገር ግን የሰው ትውልድ ቁጥር እየበዛ በሄደ መጠን በአንጻሩ የሚታየው ሥርጭት እየሰፋ መሄዱም የታወቀ ነው፤ በዚህም ምክንያት ሰዎች የተሻለ ኑሮን በመፈለግ ከቦታ ወደ ቦታ ባለማቋረጥ መፍለስና መሥፈር የተለመደ ሆነ ከዚህም በመነሣት በጋራ የመኖር ዘይቤ (የቤተ-ሰብ ኑሮ ዘይቤ) እየቀረ የየአካባቢ ሁኔታ እየተፈጠረ ሄዶአል።

ኢትዮጵያውያንም በኢትዮጵያ ውስጥ በየአካባቢው የየራሳቸውን ማኅበረሰብእ ፈጥረው ኑረዋል፤ ከዚህም ማኅበረሰቦች አንዳንዶች ደግሞ በአንጻሩ በዚህ ዓይነት መልክ ተጠናክረው ለመግኘት ያልቻሉ እንደነበሩ ይታወቃል። እንግዲህ አጠቃላይ የሰው ልጅ እንቅስቃሴ (ፍልሰት) ተለዋዋጭ ስለሆነ በዚህ አካባቢም የራሱን ተፅእኖ ፈጥሯል። ስለዚህ አንዳንዶቹ ድክመት የሚታይባቸው አካባቢዎች ከውጭ ለመጡ ታይሎች እጃቸውን በመስጠት ሥልጣናቸውን በማስረከብ የውጭን ባህልና ቋንቋ በመውረስ ብቻ ሳይወሰኑ የአካባቢዎቹንም ስሞች መለወጥ ማጨታ ሆኖባቸዋል በሌላ በኩል ግን ከጥንት ጀምሮ እንደማዕከል (ለዓባይ ወንዝ መነሻ) ሁኖ ትታይ የንበረችው ኢትዮጵያ ዘለክሰም ዳር ድንበሯን በመጠበቅ ለውጭ ታይል ሳትንበረከክ ነፃነቷን ባህሏንና ቋንቋዋን እንደጠበቀች ትገኛለች።

ዩተሷይ በክርስቶስ ልደት አካባቢና ከዚያም ወዲህ የተነሡ ሲታውንት ስለ ኢትዮጵያውያንና ስለኢትዮጵያ ቋንቋ ባህል ስለክርስትና እምነትና ስለ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ወዘተ በሚኖሩበት ጊዜ ስለኢትዮጵያ ዘለክሰምና ስለሕዝቦቿ መሆኑ ሳልቶ እንደሚታይ አያጠራጥርም። እንግዲህ ታሪካዊ ተጨባጭ ሁኔታ ይህ ሆኖ ሲገኝ የአሜሪካን መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ኢትዮጵያን ብሉዳን ፣ ኢትዮጵያዊን ኢትዮጵያውያንን በሱዳናዊና ሱዳናውያን በጥቁር ሰው በሱዳን ሕዝቦች ተክቶ መናገር ምን ማለት ነውየ ብመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ሱዳን ኢትዮጵያ አልነበረም ማለት አይደለም ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ኩሽ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ አይሸፍንም ማለት አይሆንም ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ "ኢትዮጵያ" ሲል ብዙ ጊዜ የሚናገረው ከግብጽ ደቡብ እስከ ሕንድ ድረስ ያለውን አካባቢ ሲሆን በዚህ ክልል የሚገኙት ደግሞ በማያሻማ ሁኔታ ኢትዮጵያና ሱዳን ናቸው።

ሱዳን የሚለው ስም ከግሪብኛ ቋንቋ የመጣና ትርጉሙም ጥቁር ማለት እንደሆነ ይነገራል ሱዳን አሁን ልሆነበት አካባቢ ቆይቶ የተሰጠ ስም እንደመሆኑ መጠን በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በጥንት የታሪክ ሠነዶች የተወሳበት (የተጠቀሰበት) ጊዜ አይታይም ዛሬ ሱዳን ተብሎ የሚጠራው አካባቢ በመሰስተኛ አካባቢ ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ እንኳን ሳይሆን በታሪክ ኑቢያ ይባል እንደ ነበርና ከተማው አስቀድሞ ኖፕታ ጥይቶ መርዌ እንደነበር ይታመቃል። ስለዚህ ኢትዮጵያን በሱዳን ተክቶ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ ውጭ (ከጥንቱ የታሪክና ቅዱሳት መጻሕፍት ኢትዮጵያ ውጭ) አድርጎ መመልከት ታሪክን ብቻ ሳይሆን ራሱን መጽሐፍ ቅዱስን ማስተባበል ነው።

በታሪክም ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ ሲመለስ "ኩሽ" "ኢትዮጵያ" ተብሎ መተርጎሙን አውስተናል ብሉይ ኪዳን በግሪክ ቋንቋ ከተተረጎመበት ጊዜ ጀምሮና ከዚያም ወዲህ የተተረጎመቸው ቋንቋዎች የአካባቢን ቅርፅ ማካለል ቀርቶ ኢትዮጵያ የሚለውን ስም የለመጡበት ቦታ አይተኝም ለምሳሌ የጥንት ቋንቋዎችን መጥቀስ ቢያስፈልግ ከዕብራይስጥ "ኩሽ" ቀጥሎ ራሱን ግሪክን ላቲንን(ሮማይስጥ) እና ግእዝን ከጉድኒውስ ባይብል ጋር አነጻጽሮ መመልከት ይቻላል። ስለዚህ የሚከተሉትን ጥቅሶች መመልከት ኢትዮጵያን ሱዳን ብሎ ለተረጎመው ለተዛባ አመለካከት በቂ ሊሆን ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱስ		የጥንት ቋንቋዎች		ጉድኒውስ ባይብል	
ጥቅሶች	ዕብራይስጥ	ግሪክ	ላቲን ሮማይስጥ	ግእዝ	ጉድ ነውስ
ዘሁልቁ 12፡1	ኩሽ	ኢትዮጵያ	ኢትዮጵያ	ኢትዮጵያ	ሱዳን
2ተኛ ነገሥት 19፡9	>>	>>	>>	>>	>>
2ተኛ መዋዕል 12፡3	>>	>>	>>	>>	>>
2ተኛ ዜና መዋዕል14፡9	>>	>>	>>	>>	>>
2ተኛ ዜና መዋዕል16፡8	>>	>>	>>	>>	>>
መጽሐፍ ትዱስ		የጥንት	ጉድኒውስ ባይብል		

		ቋንቋዎች			
ጥቅሶች	ዕብራይስጥ	ግሪክ	ላቲን ቮግይስጥ	ግእዝ	ጉድ ኑውስ
አስቴር 1፡1	>>	>>	>>	>>	>>
አስቴር 8፡9	>>	>>	>>	>>	>>
ኢዮብ 28፡19	>>	>>	>>	>>	>>
መዝሙረ ዳዊት 66፡ 31	>>	>>	>>	>>	>>
መዝሙረ ዳዊት 87፡4	>>	>>	>>	>>	>>
ኢሳይያስ 18፡1	>>	>>	>>	>>	>>
ኢሳይያስ 11፡11	>>	>>	>>	>>	>>
ኢሳይያስ 20፡3	>>				
ኢሳይያስ 20፡4	>>				
ኢሳይያስ 20፡5	>>				
ኢሳይያስ 37፡9	>>				
ኢሳይያስ 43፡3	>>				
ኢሳይያስ 45፡14	>>				
ኤርሚያስ 13፡23	>>				
ኤርሚያስ 38፡7	>>				
ኤርሚያስ 38፡10	>>				
ኤርሚያስ 18፡12	ቡሽ	ኢትዮጵያ	ኢትዮጵያ	ኢትዮጵያ	ጥቁር ሰው
ኤርሚያስ 46፡9	>>	>>	>>	>>	ሱዳን
ኤርሚያስ 39፡16	>>	>>	>>	>>	>>
ሕዝቅኤል 30፡4	>>	>>	>>	>>	>>
ሕዝቅኤል 30፡9	>>	>>	>>	>>	>>
ሕዝቅኤል 38፡5	>>	>>	>>	>>	>>
ዳንኤል 11፡43	>>	>>	>>	>>	>>
አሞጽ 9፡7	>>	>>	>>	>>	>>
ናሆም 3፡9	>>	>>	>>	>>	>>
ሶፎንያስ 2፡12	>>	>>	>>	>>	>>
ሶፎንያስ 3፡10	>>	>>	>>	>>	>>
ዘፍጥረት 2፡12-13	>>	>>	>>	>>	>>
ግብረ ሐዋ. 8፡36-39	>>	>>	>>	>>	>>

በተስታይ የተጥቀሳሙባቸው ሌሎች ቋንቋዎች ከአንዳንድ የተወሰኑ አጋጣሚዎች ከለሌሆነ በስተቀር ይህንኑ መንግድ ተከትለው ነው የሚገኙት። ለምሳሌ የተመለከትናቸውን የንጉሥ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ (KJB) የተሻሻለው መደበኛ ትርጉም (RSV) የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (JB) እና ሕያው መጽሐፍ ቅዱስ (LB)(የተባሉትን ትርጉሞች) የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጎሞችን ከጉድኒውስ ባይብል ጋር አነጻጽሮ ቀጥሎ ውመወልክት ይቻላል።

ምሳ ቁጥሮች	KJB	RSV	JB	LB	GNB
ይሁዳ ዜና መዋ.12፡3	ኢትዮጵያውያን	ኩሻውያን	ኩሻውያን	ኢትዮጵያውያን	ሱዳናውያን
አስቴር1፡1	>>	>>	>>	>>	>>
መዝ.-	>>	>>	>>	>>	>>
ኢሳይያስ 18፡1	>>	>>	>>	የዐዋጅ መንዝ የላይኛው መዳረሻ	
ኤርምያስ 13፡23	>>	>>	ኢትዮጵያዊ	ኢትዮጵያውያን	ጥቁር ሰው
ሶፎንያስ 2፡12	>>	>>	ኢትዮጵያዊ	>>	የሱዳን ሕዝብ

ስለዚህ በአጠቃላይ ከላይ ያተመለከትት ጥቅሶች ምንም እንኳን ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ከይዘትና ከቅርጽ አንጻር አንድ ጊዜ ሰፋ ባለ ትርጉም ሌላ ጊዜም ጠበብ ባለ ትርጉም ሊታይ ቢችልም ሁለት መሠረተ ሐሳቦች ደግሞ ከዚህ ሃይት ጋር የማይነመዱ ቸነው ይታያሉና ለምን? የሚለው ጥያቄ ሥነ አእምሮ ሊመልሰው የማይችል ጥያቄ ነው ማለት ለምሳሌ ኢትዮጵያ "ኩሽ" የዐባይ ወንዝ መነሻ መሆኗ በትክክል ሲታወቅ ማኅበሩ ከላይ የጠቀስናቸውን ጥቅሶች በአጠቃላይ ኢትዮጵያን ሱዳን ኢያለ ሲተረጉም የዐባይ ወንዝ ከኢትዮጵያ (ኩሽ) ይነሣል የሚለውን ዐረፍተ ነገር ነገር ነው ሙሉ

በዕብራይስጡ እንዳለ ከኩሽ ይነሣል በማለት መተርጎሙ ግራ ከማጋባት አያልፍም። ስለዚህ "ኩሽ" የሚለውን ቃል በሌሎች ክፍሎች "ሱዳን" ብሎ ተርጉሞ በዚህኛው ጥቅስ ኩሽ ብሎ ማስቀመጥ የተፈለገበት ምክንያት ግልጽ አይደለም ከዚህም ጋር በሌዲስ ኪዳን (ግብረ ሐዋርያት 8፡26" ኢትዮጵያ የሚለው ስም ወዴ ሱዳን አልተለወጠም ምንአልባት በዚህ ግዝፈር አመለካከት የብሉይት ኪዳን ኢትዮጵያና የሐዲስ ኪዳን ኢትዮጵያ የተለያዩ ይሆኑ? ወይስ የብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያን ሱዳን ብለው እንዴተረጎሙት የሐዲስ ኪዳን ኢትዮጵያን የዛሬዋ ኢትዮጵያ ማለታቸው ይሆን? መልሱ የነሱ ጉዳይ ይመስላል በኛ በኩል ግን የሁሉቱም መልስ ኢትዮጵያ ናት።

ኢትዮጵያ ከግብጽ ደቡብ እስከ ሕንድ የተዘረጋው ገጸ ምድር መሆኗን ብሉያዊት ቅዱሳት እያረጋገጡ ከግብጽ ደቡብ የሚገኘውን ጠባብ አካባቢ ብቻ በመውሰድ ሱዳን ብሎ መተርጎም በታሪክ ዘንድ ተቀባይነት የለውም ስለዚህ ኢትዮጵያ የሚለው በሱዳን እየተተካ የተመለሰው መጽሐፍ ቅዱስ (ጉድ ኒውስ ባይብል) አገዘያ መቅረቡና በዓለም ላይ ለአንባቢያን መሠራጨቱ እንደተደረሰበት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራቀና የተባባ ትርጉም በመታወም ደብዳቤዎችን ለዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ማስተላለፉቸው ይታወቃል።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ለዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በመጀመሪያ በአስተላለፈው ደብዳቤ (ማላሰቢያ) ኅሐስ 17 ቀን 1977 ዓ.ም(እ-ሐ-ዘ-አ) ኢትዮጵያ ሱዳን ተብሎ መተርጎሙን በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ደንበኞችና በመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢያን ዘንድ ትችትንና ክርክርን እያስነሣ ስለሆነ ማኅበሩም በበኩሉ ቀደም ብሎ የተመለከታቸውን አራት የመጽሐፍ ቅዱስ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች በማነጻጸር ሲመለከት አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ልዩነት እንደሌላቸው ማለት ኢትዮጵያ የሚለውን ሰም የለወጠበት ወይም በሌላ የተኩበት በታ አለመኖሩን እያረጋገጠ እንደመገኘቱ መጠን ይህ ኢትዮጵያን ሱዳን ብሎ የመተርጎም ሁኔታ የመጽሐፍ ቅዱስ ወዳጆች ኢትዮጵያውያንን ያስገረመና ያስቆጣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበሩም በዚህ ትርጉም ላይ የሚዘንበብትን ጥያቄዎች ለመመለስ ያልቻለና የተሳሳተ መሆኑ አጥጋቢ ምክንያት ያበለ መልስ ካልተገኘ በስተቀር ነባሩ ይህን መጽሐፍ ቅዱስ (ጉድ ኒውስ ባይብል) ማሳተፉሉን የሚገቱ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያውያን ዓይን ዘንድ የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርን ታማኝነት ከዋርጣሬ ላይ እንደሚጥል የደረበትን ፍርሃት በመግለጽ አጥጋቢ መልስ በተቻለ ፍጥነት እንዲሰጠው ጠይቋል። ስዚህ ደብዳቤ የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የሰጠው መልስ (መስከረም 19 ቀን 1977 ዓ/ም እ-ኤ-ዘ-አ) በአጭሩ እንደሚከተለው ነው።

"እስከ ዛሬ ድረስ በዕብራይስጥ ኩሽ የሚለው ቃል ኢትዮጵያ በመባል እየተተረጎመ የመጣ ይህም ልምድ ሰብዓ (70) ሊቃናት ይህን የዕብራይስጥ ቃል ኢትዮጵያ ብለው ከተረጎሙበት ጊዜ ጀምሮ የመጣ ልምድ ቢሆንም ነገር ግን በዕብራይስጥ ኩሽ የሚያመለክተው የዛሬ ኢትዮጵያን በግልጥ ሳይሆን ሁል ጊዜ በግምት ከዛሬ ሱዳን ጋር የተቀራረበ አካባቢን ወይበልጥም ኑቢያን እንደ ነበር ሕዝቅኤል 29: 10 ግልጥ በሆነ ሁኔታ እንደሚጠራው ኩሽ በግብጽ ደቡብ ድንበር የሚገኘው አካባቢ ስለነበር የዛሬ ኢትዮጵያን ይሸፍን ነበር ለማለት እንደማያስችል በመዝግብተ ቃላትና በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅደረ ቃሉት ኩሽና በግብጽ ደቡብ የሚገኘውን አካባቢ በወላ ውረድ የዛሬ ሱዳንን የሚሸፍን አካባቢ መሆኑን እንደሚወስኑ እንደዚሁም ኩሽ በክፍተኛ የሥልጣን ቁንጮ ላይ በሚገኝበት ወቅት በአራተኛው ፈሳሽ አጠገብ የሚነሱው ናፕታ ኩተማው እንደ ነበር ቍይዶ ኩተማው በአምስተኛው ፈሳሽና በካርቱም መካከል ማማሽ መስመር ላይ ወደሚገኘው መርዌ እንደተዛወረ እንደሚያመለክቱ አስተያየቱንና አጭሙን ከገለጸ ብኋላ በሚከተለው ዓይነት የተለያዩ አማራጮች ተሞክረው እንደ ነበር በመጨረሻ ሱዳን ብሎ መተርጎሙ የተሻለው አማራጭ መሆኑን አመልክተዋል።

* ኩሽን ላይለወጥ - ሳይተረጉም መውሰድ (ገልብጦ መውሰድ) ግን ትርጉም የለሽ በመሆኑ አልተወሰደም
* በአጠቃላይ ኢትዮጵያን መውሰድ (ኢትዮጵያ ብሎ መተርጎም) ግን አዲስ ኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ኩሽን ስለማትሸፍን አልተፈለገም
* ኑቢያ ብሎ መተርጎም ግን ዛሬ ኑቢያ ብሔራው ህልውና የሌላት ሀገር መሆኗን አልተመረጠም።
* ሱዳን ብሔራዊ ህልውና ያለውና ኪሴሎች የአፍሪካ አገሮች ይልቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ኩሽ ለሚለው ስም የተቃረበ ምጉክ ሆኖ ስለሚገኝ ተመርጧል።

ቅጥሎም ይህን ኩሽ የሚለውን ስም በመተርጎም ሪነድ (NEB) አስቴር 1፡1 8፡9 ኢዮብ 28፡19 ኢትዮጵያ መዝሙረ ጻዊት 66:3፣ ኢሳይያስ 43:3 45:14 ኤርሚያስ 13:23 ኑቢያዊ ከሌሎች ቦታዎች ኩሽ ኩሻዊ በማለት እንድወጥ ባልሆነ መንገድ እየተተረጎመ ለገለፀ በቂላ እንግሊዘ በጉድ ኒውስ ባይብል ለማድረግ የተሞክረው በመጽሐፍ ቅዱስ የተመለከተ አካባቢን ከዘመናው አንግለዝኛ ቋንቋ ቃል መልክዐ ምድራዊ ስያሜ ጋር በታቻለ መጠን ማቃረብ ነበር፣ ለምሳሌ ከዚህ ጋር የሚመሰል ሁኔታ በግብረ ሐዋርያት 27:27 በግሪክ ቋንቋ አድርያቲክ ባሕር የሚለው ዛሬ አድርያቲክ ተብሎ የሚታወቀው ቦታ መርከብ በማዕበል ጊዜ የሚቆምበት ቦታ አይደለም ስለዚህ ጉድ ኒውስ ባይብል ይህን ቦታ ሚድትራንያ ብሎ ይጠራዋል።

ስለዚህ ይህ አገላለጥ በዚህ ጉድኒውስ ባይብል ቁጣና ቅሬታ ለተሰማቸው አንባቢያን መልስ ይሆናል የሚል ተስፋ አለን" ይላል። ይህ አሁን የተመለከተው ምሳሌ ከዋያቄው ጋር አብሮ የሚሄድ ምሳሌ ይሆናል ብሎ መቀበል በጣም አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም ኢትዮጵያና ኩሽ በዚህ ምሳሌ ሊንጸሩ አይችሉም። የአጠራር ለውጥና የህልውና ለውጥ አንድ ነው በሚል መልክ ምሳሌ ሁኔው ማገለግል አይችሉም።

አሁንም የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ኪንያ ለሚገኘው ለዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ደብዳቤ (ሚያዚያ 10 ቀን 1979 ዓ/ም እ-ኤ-አ-) ጽፎአል። በዚህም ደብዳቤ ምንም እንኳን የተሰጠው መልስ አጥጋቢ መሰለ ቢታይም ከእውነተኛው ፍሬ ነገር በመነጣጠል ብዙ ሰዎች ይህን ልዩነት ለማመልከት የተለያየ አስተያየትን ለማድረግና ቅሬታዎችን ለመግለጽ የተገደዱ በመሆናቸው ሁኔታው ወደ ፓስቲክስ እያዘነበለ እየሄደ በመታየቱ ዋናው አስተዳደር ኮሚቴው በአዳረገው ስብሰባ ሚያዝያ7 ቀን 1979 ዓ/ም እ-ኤ-አ-) በፍጥነት ይህ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይሰራጭ ለማቆምና ሁኔታውን ለጠቅላላ ቦርድ ለማቅረብ ያደረገውን ውሳኔ በማምጣ ቤትም 2000 ቅጅ እንዲ አለ ይህንም ምን ማድረግ እንዳለበት የቦርዱን ውሳኔ የሚያስታውቅ መሆኑን ገልጸ ነበር።

ለዚህ ደብዳቤ የተሰጠው መልስ (ማርች16 ቀን 1979 ዓ/ም እ-ኤ-አ-) ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ትርጉም ንኡስ ኮሚቴ ውይይት እንደተደረገበትና ውጤቱም እንዲገለጽ የተወሰነ ስለሆነ ይህ ወረጃ (መግለጫ) በቅርቡ እንደሚደርስና ጉዳዮን በተመለከተ አጥጋቢ መግባባትን እንደ ሚፈጥር ያለንን እምነት የሚገልጽ ነበር። የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ጉዳዩን በማመዛዘን ይመለሳል ቅይቶ ለቀረበለት ሚለታውሻ ብሰጠው መልስ (መስከረም 25 ቀን 1979 ዓ/ም እ-ኤ-አ-) ችግሩ ከልምድ ጋር ተያይዟል ይህም በትክክል የተሳሳተ ግንዛቤን ችግርን ፈጥሮአል ስለዚህ "ኩሽ" ከኢትዮጵያ ይልቅ ሱዳን ብሎ ለመተርጎም የሚያነሣሣ የመጽሐፍ ቅዱስና ወይም የታሪክ አመንታ (ምስክርነት) ቢኖር ኑሮ ይህን ዓይነት ለውጥ ማድረግ ደስ ባለን ነበር ነገር ግን በተደረገው ማንኛውም ምርምር ድርጊቱ ወደ ስሕተት ያመራ መሆኑን ነው ለመግንዘብ የቻልነው በግለት አጭመን ለመግለጽ ሞክሮአል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን ቅዱስ ሲኖዶስ በዚህ ጉዳይ ላይ ስብሰባ አድርጎ ኅዳር 9 ቀን 1979 ዓ/ም እ-ኤ-አ-) ነኖ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የቦርድ ስብሰባ ግንቦት 25 ቀን 1971 ዓ/ም የጉድኒውስ ባይብል ጎበኝል አለመሆኑን መልስ ተመልክተዶል 2ኛ ይህንን መጽሐፍ ቅዱሰ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር እንዳደረገው ሁሉ ከእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ጋር በድጋሚ አመሳክሯል።

በዚህም ጊዜ ይህ ድርጊት የሚያስገርምና የሚያሳዝን ድርጊት ሆኖ አግኝቶታል በአጠቃላይ ሲታይ በነቢያት ትንቢት በሐዋርያት ትምህርት የታወቀች ኢትዮጵያን ሐዲሙና ሰመክድ፣ የኢትዮጵያውያንን እምነት ለማናጋት የተፈጠረ በአጠቃላይ የንበረንና የታውቀን ጥንታዊ ታሪክን እምነት እንደአልነበረ ለማድረግ ሆነ ተብሎ የተፈጸመ ድርጊት ሆኖ በመገኘቱ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በሙሉ በዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ላይ ፈጽሞ እምነት የማያስጥል የጠፋትነት አቋም መሆኑን ለመግንዘብ ስለቻሉ ስለዚህም የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ለኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በሰጠው መልስ (መስከረም 19 ቀን 1987 ዓ/ም እ-ኤ-አ-) የሠፈረው አመልካከት (ሐሳብ) ከጉድኒውስ ባይብል የተለየ ሆኖ ባለመግኘቱ ጉድኒውስ ባይብል ኢትዮጵያን ሱዳን ኢትዮጵያንን ሱዳናውያን እያለ ያተመው ንና ያሳተመውን አስቦበት ከአላሰረመ በስተቀር ጥንት የነበረውን እየሰረዘ ሌላ የሚያሳትም ከሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱም ሆነች አገራቱን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበሩ ላይ እምነት ስለማይኖረው በዚህ ርዕስ የታተመውም መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም አገር እንዳይሠራጭ ወደፊትም እንዳይታተም እንዲያደርግ በዚህም የማይስማማና ስሕተቱንም የማያርም ከሆነ ግን በየትኛውም የዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ቅርንጫፍ የሚታተመው መጽሐፍ ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባና ሕዝቡ እንዳይቀበለው በማንኛውም የአገሪቱ ክፍል እንዳይሰራጭ በሕግ ለማሳገድ መወሰኑን (ቦር 6 ቀን 1987 ዓ/ም እ-ኤ-አ-) ለሚከተሉት ማኅበራት አስተላልፎአል።

- ለዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት በሙሉ
- ለዓለም አቀፍ የእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
- ለአፍሪካ መጽሐፍ ክርስቲያኖች ማኅበር
- ለዓለም ሉተራን ፌደሬሽን

የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርም ይህ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እንደ ደረሰው ጉዳዩ በማም ጥልቀት ባለው ሁኔታ እንዲመረመርና የሚደረስበትም ውጤት ወደፊት እንደሚገለጽ በማረጋገጥ ያለውን ምኞት (መጋቢት 12 ቀን 1987 ዓ/ም እ-ኤ-አ-) ገልጸአል። ይህ ማኅበር በሚቀጥለው ደብዳቤ (ሐሰሴ 5 ቀን 1987 ዓ/ም እ-ኤ-አ-ስ) የትርጉም አከሰፕተሮች ልዩ ኮሚቴ በትክክል ጉዳዩን እንደመረመረና ከሙሉ ውይይት በሒሳም በደረሰበት የውሳኔ ሐሳብ በዕብራይስጥ ኩሽ ተብሎ የተመለከተው መልክዕ ምድራዊ አካባቢ የዛሬውን ሱዳን ድንበሮች አልፎ (ተሻግሮ) የሚሄድ በመሆኑ በተሰማማበት መሠረት ኩሽን ቁይም ኢትዮጵያን ይዞ መሄድ በትርጉሜ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ቢሰማም ነገር ግን ኩሽ ምንም እንኳ የማያሻማ ሆኖ ቢተኘም አቅማመጡ ለማዞሮች እንበቢያን ያልታወቀና ያልተሰመደ ስለሆነ ሊመረዋ እንደአልቻለና ምክንያቱም በዕብራይስጥ ኩሽ የዛሬ ኢትዮጵያንና የዛሬ ሱዳንን የሚሸፍን ከግብጽ ደቡብ ያለው አካባቢ ስለሆነ ይህን ዐግርጌ ማስታወሻ በማስቀመጥ ኢትዮጵያን ትክክለኛ ትርጉሙ መሆኑን ይዞ መሄዱ ተቀባይነት ያለው ስም መሆኑን ለማረጋገጥ ጥሯል።

ይህ የውሳኔ ሐሳብ በአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዓለም አቀፍ ትርጉም ኮሚቴ ንኡስ ኮሚቴና በአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የአስተዳዳሪዎች ቦርድ የጋራ ስብሰባ ከተመረመረ በኋላ ወደ ፊት በሚደረጉት ሕትመቶች ኢትዮጵያ የሚለው ስም እንደሚታተም በአንድ በኩል ሲያረጋግጥ በሌላ በኩል የአሁኑ ሕትመት ቅጅ ብዛት ያለውና እየተሠራጨ እንደመሆኑ መጠን አዲስ ሕትመት ለማድረግ ያለው ቅጅ ተሸፋፍኖ እስከ አለቀ ድረስ በርከት ያለ ጊዜ የሚወስድ መሆኑን ገልጸአል።

በአጠቃላይ ከብዙ ደብዳቤዎችን የአሳብ ልውውጦች ቤሓላ ጉዳዩ ከዚህ መደምደሚያ ላይ መድረሱ በመጠኑም ቢሆን አጥጋቢ ሆኖ ይሰማል ነገር ግን ከላይ የተመለከትነው የአሳብና የደብዳቤ ልውውጥ በመጨረሻ የተደረሰበት ውሳኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና በተጠቀሱት ማኅበራት ጽሕፈቶች ማኅደሮች መገኘብ ይህ መጣጥፉ ብቻ ቢቂ ሆኖ አልታየም ምክንያቱም ይህ ትርጉም በብዛት የታተመና በመላው ክፍላተ ዓለም የተሰራጨ እንደመሆኑ መጠን በሚልዮን ለሚቆጠሩ አንባቢያን የተሳሳተ የታሪክና የመልክዐ ምድር ግንዛቤ ያስጨበጠ መሆኑን ለማስረዳት ተጨማሪ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተግኝቷል።

ስለዚህ አስክአሁን በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት አንደኛ "ኩሽ" ወይም "ኢትዮጵያ" የሚለው የብሉይ ኪዳን ቃል አሻሚ ትርጉም የያዘ ሆኖ መታየት የለበትም ኩሽ ወይም ኢትዮጵያ የጥንት ታሪክና የመልክዐ ምድር ሊቃውንት አስተሳሰብንም ጨምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ የአካባቢያችን አጠቃላይ ስም ሲሆን ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያውያንም የአካባቢው ዘርን ትውልድ ስም ሆኖ ነው የሚገኘው(የሚታየው) ሁለተኛው ኩሽ ወይም ኢትዮጵያ ከላይ እንደተነገረው የአካባቢ የጋራ ስም ሆኖ እንደ ነበረ ይነገር እንጂ ቀስ በቀስ በውስጡ ሌሎች የአካባቢ ስሞች ተክሥተዋል። ለምሳሌ ቀዳም ብሎ አክሱምን በተጨማሪ ኑቢያን መጥቀስ ይቻላል ሆኖም ኢትዮጵያ ዘአክሱም የሚለው አካባቢ የነበረውን ስምና የፖለቲካ ዳር ድንበር ሊይቶ ሲተዋል እንደ ኑቢያ ያሉት ግን የአካባቢ ስማቸውን በመለወጥ ለምሳሌ ኑቢያ "ሱዳን" በመባል ልትጠራ ትችላላች።

እንግዲህ ኩሽ ወይም ኢትዮጵያ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ምንም እንኳን በማብጽ ደቡብ አስክ ሕንድ ያለውን አካባቢ ይሸፍን እንደነበር ቢነገርም የበለጠ ንልጭ የሚታየው የዛሬይቱ ኢትዮጵያንና ሱዳንን እንደሚሸፍን ነበር። ስለዚህ ኩሽ ወይም ኢትዮጵያ ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ ሱዳንንም እንደሚሸፍን አድርጎ መናገር ትክክለኛ መሆኑ ሲታወቅ ኩሽን በሱዳን ተክቶ(ተርጉሞ) መናገር ግን የዛሬዋ ኢትዮጵያን ከጥንት ኢትዮጵያ ውጭ ስለሚያደርጋት የተሳሳተ ግንዛቤ ሆኖ ነው የሚገኘው። እንግዲህ ይህ ዓይነቱ አመለካከት (ኢትዮጵያን ሱዳን ማለት) ከቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ጋር ተገናዝቦ አይገኝም።

በአንድ በኩል ታሪክን ከሥር ከመሠረቱ የሚያናጋ ሆኖ ሲገኝ በሌላ በኩል ደግሞ የአንድን ታሪካዊ አገር ህልውና የሚነካ ሆኖ በመገኘቱ በጣም የሚያሳዝንና የሚያሳስብም ነው። ስለዚህ ታሪክን ማዛባት የአገርን ህልውና መንካት ሕዝቡን ከትዝብት ላይ መጣልና ብአገር ላይ የጠላትነትን ስሜት መፍጠር ሆኖ ነው የሚታየው ምንአልባት ይህን የመሰለው ሁኔታ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ሐቅነቱን ሰቆ አንድ ወይም ሌላ አገር ከሚከተለው የፖለቲካ መንፈስ ጋር ተያይዞ ይሆን? የሚል ጥርጣሬ እስከትፈል ምክንያቱም ለብዙዎች ትርጉም ይህን መስሎ ከመታየቱ አልፎ ሌላ ምክንያት በሚንቅሳት ውስጥ ሲጉላላ አልቻለም ለ3ሺህ ዓመታት ያህል ከቅየ በኋላ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ታላትና መልክዐ ምድር ትርጽ አዲስ ግንዛቤ ተከሥቶ ይሆን? ለዚህም የሚረዳ ፍንጭ ስለአልተመለከተ ውጤቱ የግንዛቤ ለውጥ ላይሆን የዕንቅልሽ ዘይቤ ሆኖ ነው የሚታየው።

ነገር ግን ይህን የተሳሳተ ትርጉም ለማስተካከል የተሰነዘሩት ሐሳቦች እንዳተጠበቁ ሁነው በአሁን ጊዜ ሁለቱ አህተማማኝ አገሮች (ኢትዮጵያና ሱዳን) የየራሳቸውን የፖለቲካ ክልልና ሥልጣን ይዘው በጭቅርና በሰላም የሚገኙ አገሮች መሆናቸው ግልጽ ነው ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ በታሪክና በመልክዐ ምድር ሊቃውንት አመለካከት ሁለቱም አገሮች የጋራ (የወል) "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም ነበራቸው ይህም ማለት የቀየ የጋራ ታሪክ የነበራቸው መሆኑን ትክክለኛ ግንዛቤ ለመስጠት እንጂ የአሁኑን የሁለቱን አሕጉማማች አገሮች ተጨባጭና የታሪክ ውጤት የሆነውን የፖለቲካ ሕልውናቸውን ሁኔታ የሚመለከት ጉዳይ ሆኖ ሊተረጉም አይቻልም።

የዛሬዋ ኢትዮጵያ የቅዱሳት መጻሕፍት የታሪክና የምን ጥንት ኢትዮጵያ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ
ነሐሴ 1982 ዓ. ም